# ቀስተደመና ሬድዮ

ትችት 24.01.03

## የርሃብ ዘር ተዘርቶ ርሃብ ሲመረት

ከዛሬ ሁለት አመት በፊት ፕሮፌሰር ሾሱዶብስኪ የተባሉ በካናዳ የኦቶዋ ዩኒበርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ስለሚከሰተው ርሃብ አንድ ጥናት አሳት መው ነበር። ይህ በመስከረም ወር 1993 እ.ም. ዘ ኢኮሎጂስት በተባለው መጽሄት የታተ መ ጥናት ማስጠንቀቂያ አዘል ጥናት ነበር። ለጽሁፋቸው የሰጡት አርእስት ራሱ «በኢትዮ ጵያ የርሃብ ዘር ሲዘራ» የሚል አስደንጋጭ አርእስት ነበር። ፕሮፌሰሩ በዚህ ጥናታቸው በአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋዋማት፤ ዩኤስኤይድ በተባለው የአሜሪካን መንግስት የተራድኦ ድርጅት፤ በግዙፍ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች፤ በወያኔ መንግስትና በህገወጥ የንግድ ተቋዋም ቹ ርኩስ ትብብር የኢትዮጵያ ገበሬዎች እንዴት እጅግ ዘግናኝና አጥፊ ወጥመድ ውስጥ እየገቡ በመሄድ ላይ እንዳሉ ያሳያሉ። እጅግ ስብጥርጥር ሆኖ በአለም ደረጃ የተደነቀው የሃገራችን ህይወታዊ ሃብት (ባዮዳይበርሲቲ) እንዴት በመውደም ላይ እንዳለ ያትታሉ። ይ ህ ሁሉ የሚፈጸመው ነጻ የገበያ ኢኮኖሚ በሚሉት ፈሊጥና ርሃብን ለመዋጋት በሚል ስበ ብ እንደሆነ ያስረዳሉ። የጽሁፋቸው መነሻ ከጥናቱ ሁለት አመት ቀደም ብሎ በ1990 እና በ1991 እ.ም. በሃገሪቱ ገባ የተባለውና ስምንት ሚልዮን ገበሬዎችን ለአደጋ ዳርጎ የነበረው ርሃብ ነበር። ፕሮፌሰሩ የዚህን ርሃብ ምክንያት በመተንተን አይወሰኑም። በምድራችንና በ ህዝባችን ውድመት ላይ ያነጣጠረው የነዚህ አጥፊ ሃይሎች ርኩስ ቃልኪዳን እስከቀጠለ ድረስ ሌሎች ርሃቦች አይቀሬ ናቸው ብለው ይተነብያሉ። ርሃብ ሲከሰት ይህንን ርሃብ ለ መዋጋት በሚል ሰበብ የሚወሰዱት ርምጃዎች ርሃብን የሚያባብሱ እንደሆኑ ሲጠቁሙ በወ ቅቱ ሃገሪቱ ባለችበት ሁኔታ የርሃብ እርዳታ የሚባለው ነገር መፍትሄ ሳይሆን እስከናካቴው የርሃብ መንስኤ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው ብለው ያጋልጣሉ። ጥናታቸውን ሲያጠናቅቁ

*« እንግዲህ ነገሩን በሌላ አነጋገር እናስቀምጠው። መጀመሪያ ነገር ርሃቡ በአመዛኙ ሲታይ አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት፤ የአለም ባንክና የአሜሪካ መንግስት ለግዙፍ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ጥቅም ሲሉ በሃገሪቱ ላይ የጫኑት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውጤት ነው። እ ነዚሁ የባዮ ቴክኖሎጂ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች እንደገና በዚህ ርሃብ በመጠቀም የኢት ዮጵያን ህይወታዊ ሃብት (ባዮዳይበርሲቲ) በይበልጥ ሸረሸሩት። በልማድ የነበረውን የገበሬ ከገበሬ የዘር መለዋወጥና መበዳደር አሰራር ሆን ብለው አፈራረሱት። በመንደር ደረጃ ተ ቋዋቋመው የነበሩት የዘር ማትረፊያ ጎተራዎች ወይም ባንኮች በመጤና በተቀየሩ ዘሮች እ ንዲሞሉ ተደረገ። እነዚህ መጤና የተቀየሩ ዘሮች ከምግብ ርዳታ ጋር ተደባልቀው ለድሃ ገበሬዎች እንዲታደሉ ተደረገ። የአለም የምግብ ፕሮግራምና የዩኤስኤይድ የአስቸኩዋይ ር ዳታ የተቀየሩ ዘሮችና የማዳበሪያ «ስጦታዎችን» ማካተት ጀመሩ። ይህ ደግሞ ለግዙፎቹ የእርሻና የባዮቴክኒክ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የግብርና ህይወት ውስጥ ሰርስ ረው እንዲገቡ መንገዱን ጠረገላቸው። እነዚህ ርዳታዎች ለርሃቡ መፍትሄ አይደሉም። የ ርሃቡ መነሾ ናቸው። ሆን ተብሎ ገበሬው የነዚህ መጤ ዘሮች ጥገኛ እንዲሆን በመደረጉ ለቀጣይ ርሃቦች መድረኩ እየተዘጋጀ ነው።አንድ ሚልዮን የሚገመት ህዝብ ረገፈበት ከተ ባለው የዛሬ አስራ አምስት አመት ተከስቶ ከነበረው ርሃብ በሁዋላ አሁን ደግሞ በሃገሪቱ ላይ ሌላ አስከፊ ርሃብ እያንጃበበ ነው ተብለናል። ዛሬ ግን ስምንት ሚልዮን ኢትዮጵያው ያን ለርሃብ ተጋልጠው ስናይ ችግሩን በአየር ጠባይ ላይ ብቻ መላከክ እንደማይቻል እና ውቃለን።»* በማለት ፕሮፌሰሩ ትንቢታዊ ጽሁፋቸውን ደምድመዋል። እንደተነበዩትም ይኸ ው ዛሬ 15 ሚልዮን ኢትዮጵያውያን ላይ ያንጃበበው ርሃብ ተከስቱዋል።

ፕሮፌሰሩ በዚህ ጥናታቸው ገና ወያኔ ሃገሪቱን ሲቆጣጠር ጀምሮ በነጻ ገበያ ስም በ ነዚህ አለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋዋሞች ግፊት ስለተደረጉት ለውጦችና ስላስከተሉት የኢ

ኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ብዙ ጽፈዋል። የርሃቡን ጉዳይ በተመለከተ የሚያነሱዋቸው ዋና ዋና ነጥቦች በጥቅሉ ሲቀርቡ የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. በአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋዋማት ግፊት በሃገሪቱ ላይ በተጫኑት ለውጦች መሰረት የማዳበሪያና የዘር ንግድ ወደ ግሉ ኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲዞር ተብሎ ፓዮኒየር ሃይ በሪድ ኢንተርናሽናል በተባለው ድንበር ዘለል ኩባንያና የወያኔ ሞኖፖሊ ሆኖ የሃገር ውስጥ የሚተባበረው የኢትዮጵያ የዘር ድርጅት (ኢትዮጵያን ሲድ ኢንተረፕራይዝ) ቁጥጥር ስር እንዲገባ ተደረገ። ትንሽ ሳይቆይ ከአሜሪካ ማዳበሪያ እየተባሉ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡት ኬሚካሎች ሃገሪቱን ስላጥለቀለቁ ሃገር በቀል የሆኑ ለሃገሪቱ አፈር ይበልጥ የሚስማማ ማዳበሪያ አምራቾች ከገበያው ለመውጣት ተገደዱ። ማለትም ዛሬ በሚልዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎቻችን በማማረር ላይ እንዳሉት ለሃገራችን አፈር ይስማሙ አይስማሙ ላልተረጋገጠላቸው ማዳበሪያዎች በራችንን በርግደን ከፈትን። አንዳንዴም የገበሬው ማሳ ገና በሙከራ ላይ ላሉ ኬሚካል ማዳበሪያዎች መፈተሻ ላቦራቶሪ ሆነ።

2. በነዚህ ማዳበሪያዎች አማካኝነት እርግጥ መጀመሪያ ላይ አንዳንድ ቦታዎች ምርት ጨመረ። እነወያኔና ባእዳን አሳዳሪዎቻቸውና ተባባሪዎቻቸው ግን ይህን የምርት መጨመር ሃገሪቱ ርሃብን ለመቋዋቋዋም የምታደርገውን ጥረት ለማገዝ ሳይሆን ለማደናቀፍ ተጠቀሙበት። እንደሚታወሰው የዛሬ 18 አመት ከተከሰተው ርሃብ በሁዋላ በደርግ መንግስት ለአስቸኩዋይ ጊዜ መጠባበቂያ ጎተራዎች (ኢመርጀንሲ ግሬይን ሪሰርብስ) በያለበት በሃገሪቱ ተቋዋቁመው ነበር።ከእንግዲህ ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት ነገር አያስፈልጋትም ተብሎ እነዚህ መጠባበቂያ ጎተራዎች እንዲፈርሱ ታዘዘ። ኢትዮጵያ ያመረተችውን ትርፍ እህል ጎተራ ከመክተት ይልቅ ያለባትን እዳ ለመክፈል ወደ ውጭ መሸጥ አለባት ተብሎ ለምሳሌ በ1989 ኢ.ም. አንድ ሚልዮን ቶን እህል ኤክስፖርት ለማድረግ ተገደደች።

3ኛ. በሚቀጥለው አመት አይቀሬው ርሃብ ሲገባ የታሪክ ምጸት ሆኖ ይኸው ከኢትዮጵያ የተላከው እህል እንደገና ወደ ኢትዮጵያ በርሃብ እርዳታ ስም እንዲመለስ ተደረገ። በመሃል ጥንቱንም ቢሆን ይህንን እህል የገዙት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች እንደገና የአስቸኩዋይ ጊዜ ርዳታ በሚል የሸጡትን እህል ወደ ሃገሪቱ በመጫንና በማጉዋጉዋዙ ጥረት እንሳተፋለን ብለው ባገኙት ኮንትራት ሰማይ ጠቀስ ትርፍ አካበቱ።

*4ኛ. የባሰ አለ። በ1976 ቱ ርሃብ ወቅት የሚበላው ያጣው ገበሬ በርዳታ እህል ነፍሱን ካተረፈ በሁዋላ የሚዘራው ምንም አልነበረውም። እንዲህ አይነቱ የዘር መሙዋጠጥ ለሃገሪቱ ነባርና የተሰበጣጠረ ህይወታዊ ሃብት (ባዮዳይበርሲቲ) በጣም አደገኛ እንደነበረ ግልጽ ነው። የሃገሪቱ ገበሬዎች ይህንን ለመቋዋቋዋም ከጥንት ጀምሮ ገበሬ ከገበሬ ዘር መበዳደር ልማድ ነበራቸው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ደርግ ሌላም መፍትሄ አበጀ። ሲድስ ኦፍ ሰርባይባል ከሚባል ድርጅት ጋር በመተባበር በመላ ሃገሪቱ ሰላሳ ሽ ገበሬዎች የሚሳተፉበት የዘር ማትረፊያ ባንኮች እንዲቋዋቋዋሙ አደረገ። ከትውልድ ትውልድ ሃገራችንን ያቆያት ነባሩ የገበሬው የእርስ በእርስ ዘር መበዳደር ባህልና የነዚህ የዘር ባንኮች መኖር ለነጸ ተብየው ኢኮኖሚ መስፋፋትም ሆነ ባእዳን የኛን ነባር ዘርና ባዮዳይበርሲቲ አውድመው የተቀየረና ላቦራቶሪ የተቀመመ ዘራቸውን ለማስፋፋት ያላቸውን ህልም የሚጻረር መሆኑ ግልጽ ነው።በመሆኑም በባእዳን ተጽእኖና በወያኔ መንግስት ትእዛዝ የደርግ የዘር ባንኮች በ1990 እና በ1992 ኢ.ም. መሃከል እንዲፈርሱ ተደረገ። ፕሮፌሰሩ በዚህ ጉዳይ ሲጽፉ እነዚህ የዘር ባንኮች እንዲፈርሱ የታዘዙበት ድብቅ አጀንዳ መኖሩን ገልጸው ይኸውም በትናንሹ ገበሬና በመንደር ደረጃ የሚደረገውን የተጣራ ዘር ልውውጥ አስወግዶ በነሱ ቦታ ገበሬው የመጤና በነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች የተቀየሩ ዘሮች ጥገኛ የማድረግ ድብቅ አጀንዳ እንደሆነ ያስረዳሉ።*

5ኛ. በአለም የፋይናንስ ተቋዋማት ትእዛዝ ጎተራዎች ተሙዋጠው፤ በነሱው ግፊት የዘር ባንኮቻችን ፈራርሰው፤ በማዳበሪያ ስም አልባሌ ኬሚካሎች በገፍ በገበሬው ላይ እየተጫኑ ባለበት ሁኔታ ርሃብ አይቀሬ ነበር። ከአራት አመት በፊት ስምንት ሚልዮን ህዝብ ለአዲስ ርሃብ የተጋለጠበት ሁኔታ ተፈጠረ። ፕሮፌሰሩ የሚተቹት ይህንን ርሃብ ሲሆን ሁኔታውን አይተው ሃገሪቱ ለመጭ ርሃቦች እየተጋለጠች ነው ሲሉ ተነበዩ። ለምን? ምክንያ

ቱም ይህ አዲስ ቀውስ ለወያኔም ሆነ ለአለም አቀፍ ተባባሪዎቹና አሳዳሪዎቹ የሚከተሉትን ፖሊሲ ቆም ብለው እንዲመረምሩ እንዲቀይሩ ሳይሆን በይበልጥ አጠናክረው እንዲገፉበት ሁኔታዎችን አመቻቾላቸው። የወቅቱ ርሃብ ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነትም ጋር አብሮ የመጣ ነበር። በፕሮፌሰሩ አባባል በዚህን ወቅት በጦርነት በመተረማመስ ላይ ለነበሩ አገሮች ዩ ኤስኤይድ የተባለው ድርጅት ግማሽ ሚልዮን ቶን እህል በርዳታ ስም ሲሰጥ ከዚህ ውስጥ አንድ ሶስተኛው ከተቀየረ ዘር የበቀለና በሌሎች የአለም ክፍሎች ገበያ እንዳይቀርብ ተከ ልክሎ የተጠራቀመ እህል ነበር። ከዚህ እርዳታ ጋር በመደባለቅ ደግሞ በማዳበሪያ ስም አ ልባሌ ኬሚካሎች፣ ለቀጣዩ አዝመራ ዘር በማቀበል ስም የተቀየሩ ዘሮች በሰፊው ለርሃብተ ኛው ገበሬ መልሶ መቋቋቋሚያ ተብለው በገፍ እንዲታደሉ ተደርጉዋል። ፕሮፌሰሩ እን ዲህ አይነቱ እርዳታ ለርሃቡ መፍትሄ ሳይሆን የርሃቡ መንስኤ ነው ካሉ በሁዋላ ኢትዮጵ ያ ለቀጣይ ርሃቦች እየተመቻቸች ነው ብለው የተነበዩት በዚህ ምክንያት ነው።

የአሁኑም ከደርግ ጊዜ ይበልጥ አስከፊ ይሆናል ተብሎ የሚፈራው ርሃብ ውጤት ከዚህ የተለየ አይሆንም። እርግጥ የዛሬ 18 አመቱ ያህል ሰው ላይረግፍ ይችላል። ነገር ግ ን በረጅም ጊዜ መዘዙ ሲታይ ይህ ርሃብ ለሃገራችን ገበሬዎች መመለሻ የሌለው ጥፋት ሊያመጣ ይችላል።

አንደኛ/ በእርዳታ ስም ከተቀየሩ ዘሮች የበቀለና ጤናማነቱ ያልተረጋገጠ እህል በሰ ፊው እየገባ ነው። በዚህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም እንዳልነው በሁኔታው አስገዳጅነትና አስቸ ኩዋይነት ብቻ ሌላ ከጠፋ እሱን እንበላለን። ግን ደግሞ እንድንዘራው የሚሰጠንን የእርዳ ታ ዘር ለመቀበል የሚያስገድደን ምንም ነገር የለም። ከባእዳን ተመሳጥሮ የዘር ባንኮቻችን ን ያወደመው የወያኔ መንግስት ፕሮፌሰሩ የርሃብ ዘሮች ብለው የጠሩዋቸውን ዘሮች በርዳ ታ ስም እንዳይቀበል፤ በደቡብ አፍሪካዊ አገሮች እንደተደረገው የሚገባው እህል ሁሉ ተ ፈጭቶ እንዲቀርብ እንዲያደርግ ካላስገደድነው የዚህ ርሃብ መዘዝ ገና ለረጅም ጊዜ አብ ሮን ይኖራል።

ሁለተኛ. በዚህ ርሃብ በመጠቀም እነዚሁ አለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት፤ ከምእ ራብ መንግስታት ደግሞ እንደ አሜሪካና ኖርወይ ያሉ መንግስታት መሬትን የግል ሃብት የ ሚያደርግ ስርአት እንዲተከል ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ አንድ ኮሚሽን እንዲቋቋቋ ም ጠይቀዋል። የኛ ተቃዋሚ ሃይሎችም አብዛኞቹ ይህንኑ ይጠይቃሉ። ባለፈው ወር ይፋ በሆነው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ጥናት መሰረት ከገበሬው ዘጠና በመቶው ይህ የመሸጥ ና መለወጥ መብት ቢታወቅልኝ እንኩዋን መሬቴን የመሸጥ የመለወጥ ሃሳብ የለኝም ባይ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ ይልቅ በማሳየ ላይ የይዞታ ዋስትና ይሰጠኝ እያለ እየጬኸ ነ ው። በዚህ ሁኔታ ባእዳንና አንዳንድ ተቃዋሚዎች እንደሚጠይቁት በግርግር እንዲህ አይነ ቱ ለውጥ እንዲመጣ ከተደረገ ከዚህ በፊት እንዳልነው ገጠሩንም ለወያኔዎች ማስረከብ ብቻ አይሆንም። በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን ኑሮ አመሰቃቅሎ አሁንም እን ደገና ሃገራችንን ለቀጣይ ርሃቦች ማመቻቸት ሊሆን ስለሚችል ሁሉም ቆም ብሎ እንዲያ ስብ እንጠይቃለን። የዴሞክራትና የሃገር ወዳድ ግዴታችን ኢትዮጵያን ከርሃብ ለአንዴና ለሁልጊዜ ለሚያላቅቁ መፍትሄዎች መታገል እንጂ ድሮውንም ለርሃብ መንስኤ የሆኑት ፖ ሊሲዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ሸንጣችንን ገትረን መሙዋገት አይደለምና።